የሰ/መ/ቁ. 58487

መጋቢት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ አባይነሽ ገ/ህይወት - ወኪል ወ/ት ትዕግስት ደመወዝ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ እታገኝ ደሣለኝ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለሰበር የቀረበው ክርክር በፍትሐብሔር ክስ ክርክሩ ሊሰማ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ከሣሽ ወገን አልቀረበም ተብሎ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ተከሣሽ ተሰናብተዋል በተባለበት ጉዳይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74/2/ መሠረት እንደገና ክሱ እንዲታይ ሣይጠየቅ በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኙ ቀርቦ ሊታይ የሚችል ስለመሆን አለመሆኑ የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው ደቡብ ጐንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ ከሣሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች ናቸው፡፡ ተከሣሾች የነበሩት ደግሞ ሀብታሙ ጌትነት እና የአሁኗ ተጠሪ ናቸው፡፡

1ኛው ተከሣሽ ሀብታሙ ጌትነትና የአሁኗ ተጠሪ እናትና ልጅ ናቸዉ፡፡ ከሣሽ ሁለቱን እናትና ልጅ በአንድነት የከሰሷቸው ልጅየው ሰርቆ ወስዷል የተባሉትን የተለያዩ የወርቅ ጌጣጌጦች ዋጋ ብር 13,490 እንዲከፍሏቸው ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ልጃቸው ሰርቋል በተባለው ወርቅ ጉዳይ ገንዘቡን ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ የተከሰሱት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2125 መሠረት ሃላፊነት አለባቸው በሚል ምክንያት ነው፡፡ ሁለቱ ተከሣሾች ክሱ ደርሷቸው በጽሁፍ መልስ ሰጥተው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ክርክሩ ሊሰማ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ከሣሿ የአሁኗ አመልካች ባለመቅረባቸውና የአሁኗ ተጠሪም በጽሁፍ በሰጡት መልስ ሃላፊ ልሆን አይገባም ብለው ክደው በመከራከራቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ጋር በማገናዘብ መርምሮ የአሁኗ ተጠሪ ሃላፊነት የለባቸውም ወደሚለው ጭምር የገባ ቢሆንም በእርሳቸው ላይ ክሱ አይቀጥልም ብሎ አሰናብቷቸዋል፡፡ በመጨረሻም ፍርድ በሚለው የተወሰነውና መዝገቡም ሣይዘጋ የቆየው አንደኛው ተከሣሽ በጽሁፍ በሰጠው መልስ ወንጀሉን ስለመሠረቱ ማመኑ በፍትሐብሔር የቀረበበትን ክስም እንዳመነ ይቆጠራል ተብሎ በመወሰዱ ሲሆን በተሰጠው ፍርድም በክሱ ለተጠየቀው ገንዘብ ሃላፊነት አለበት ተብሎ ተወስኗል፡፡ የአሁኗ አመልካች 2ኛዋ ተከሣሽ የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ታይቶ ከክሱ እንዲሰናበቱ የተደረገበትን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ፍርድ በመቃወም በቀጥታ ለአማራ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርበው ፍ/ቤቱ

ግራ ቀኙ እንዲቀርቡ አድርጐ ክርክሩን ከሰሙ በኋላ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ የአሁኗን ተጠሪ በሚመለከት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጨረሻ አጠቃሎ በሰጠው ፍርድ ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ከሣሿ ስላልቀረቡና ተከሣሿም በጽሁፍ በሰጡት መልስ ክሱን ስለካዱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ታይቶ ተሰናብተዋል ስላለው ያነሣው ነገር ሣይኖር በቀጥታ ወደ ሃላፊነቱ ክርክር በመግባት በወቅቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ለሰረቀው ወርቅ በፍትሐብሔር በኩል ስላለው ሃላፊነት የልጁ እናት የአሁኗ ተጠሪ በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2125/1/ መሠረት ሃላፊነት አለባቸው ብሎ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 13,490 ለአሁኗ አመልካች ሊከፍሉ ይገባል በሚል ወስኗል፡፡

ቀጥሎ ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደግሞ ክርክሩን መርምሮ በሰጠው ፍርድ የደቡብ ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኗ ተጠሪ በሚመለከት የክሱን መዝገብ የዘጋው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ስለሆነ ከሣሽም የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74/2/ መሠረት የክሱ መዝገብ ይከፈትልኝ የሚል ጥያቄ ሣያቀርቡ በቀጥታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ያቀረቡት ትክክል አይደለም፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ወደ ፍሬ ነገሩ መግባት አልነበረበትም፤ ይግባኙን መቀበሉም የስነስርዓት ህጉን የተከተለ አይደለም በማለት በዚሁ ስነስርዓት ምክንያት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የአማራ ክልላዊ መንግስት የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ መሠረት የቀረበ ሲሆን ጉዳዩም ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ነው በመባሉ ግራ ቀኙ እንዲቀርቡ ተደርጐ መልስ እና የመልስ መልሱን በጽሁፍ በመለዋወጥ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡

ጉዳዩም ከህጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የደቡብ ጐንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁኗን ተጠሪ በሚመለከት የክሱን መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ነው የዘጋው ለማለት ይቻላል አይቻልም? የአሁኗን ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ነው ያሰናበታቸው የሚባል ሆኖ ከተገኘስ ከሣሽዋ የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74/2/ መሠረት የመዝገብ ይከፈትልኝ ጥያቄ ሣያቀርቡ በመጨረሻ በተሰጠው ፍርድ መነሻ በቀጥታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረቡ ስነስርዓት ህጉን የተከተለነው የሚባል ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን በተመለከተ፡-

ከሣሽ የሆኑት የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ክርክሩ በቃል ሊሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሣይቀርቡ መቅረታቸውንና ሁለተኛ ተከሣሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ በጽሁፍ በሰጡት መልስ ሃላፊ ልሆን አይገባም ብለው ክሱን ሙሉ በሙሉ በመካድ መከራከራቸውን የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጨረሻ የሰጠው ፍርድ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበው ኮፒው የሚያስረዳ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዚህ ፍርድ ላይ የአሁኗን ተጠሪ ክዶ የመከራከር ሁኔታ የተመለከተው የአሁኗ አመልካች ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀነ ቀጠሮ ባለመቅረባቸው ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ጋር በማያያዝ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በፍርዱም ላይ የጀመረው ከሣሽ ለቃል ክርክር ስላልቀረቡ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ተመርምሯል በማለት ነው፡፡ ቀጥሎም 2ኛዋ ተከሣሽ በጽሁፍም ሆነ

በቃል ሃላፊ ልሆን አይገባም ብለው ስለመከራከራቸው ከሣሽ ደግሞ በቃል ክርክሩ ላይ ቀርበው በዚህ ላይ ተቃውሞ እንዳላቀረቡ በመግለጽ 2ኛዋ ተከሣሽ ሃላፊነት የለባቸውም ብለናል በማለት ከክሱ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከዚህም የአጻጻፍና የአገላለጹ ሁኔታ እንጅ 2ኛዋን ተከሣሽ የአሁኗን ተጠሪ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያሰናበታቸው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ መዝገቡ ወዲያውኑ ያልተዘጋው 1ኛ ተከሣሽ ክሱን አምኗል ተብሎ በመቀጠሉና ፍ/ቤቱም ውሣኔ ሊሰጥበት በማቆየቱ ነው፡፡ የአሁኗን ተጠሪ በሚመለከት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት የክሱ መዝገብ ተዘግቷል ለማለት የሚቻል ሆኖ ስለተገኘ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት የሰበር ክርክር ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ተጠሪን በተመለከተ የክሱ መዝገብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ተዘግቷል የሚባል ሆኖ ከተገኘ ከሣሽዋ የአሁኗ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74/2/ መሠረት ጥያቄ በማቅረብ እንደገና መዝገቡ ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

አመልካች ይህንን ሣይፈጽሙ ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት በተሰናበቱበት ላይ በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ የሚያስችላቸው ስነስርዓት የለም፡፡ የአማራ ክልላዊ መንግስት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔም ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1ኛ/ የአማራ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 0469 ሐምሌ 5 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ